# ቤተሰብዎን ይጠብቁ

## የኮቪድ-19 ክትባትን ይውሰዱ

የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድ የእርስዎንና የሚወዷቸውን ሰዎች ደህንነት ለመጠበቅ ተመራጭ መንገድ ነው።



### ክትባት የምወስደው ለምንድን ነው?

ክትባት መውሰድ ኮቪድ-19 እናዳይዝዎ ይከላከልልዎታል። በአጭር ጊዜ ብዙ ሰዎች በተከተቡ ቁጥር በማህበራዊ ጉዳዮች መሳተፍ፣ ትምህርት ቤትና ስራ ቦታ መሄድን ጨምሮ ወደምናውቀው ህይወት በአጭር ጊዜ ውስጥ መመለስ እንችላለን።

### ሁሉም የኮቪድ-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀና ውጤታማ ናቸው?

አዎ። ሁሉም የኮቪድ ክትባቶች ለሁሉም ክትባት የሚያስፈልገውን ጠንከር ያለ ፈተና አልፈዋል። ከ75,000 በላይ ታካሚዎች በክትባት ሙከራዎች ላይ የተሳተፉ ሲሆን ክትባቶቹ ከመጽደቃቸው በፊትም ለወራት ክትትል ተደርጎባቸውል። ከክትባቱ ኮቪድ-19 ሊይዝዎት አይችልም።

### ሌሎች የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉ?

አንዳንድ ታካሚዎች መርፌ የተወጋበት ቦታ መቁሰል እና ራስ ምታት የመሳሰሉ መጠነኛ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ሪፖርት ያደርጋሉ። ክትባቱ እየሰራ መሆኑን የሚያሳዩ የጉንፋን አይነት ምልክቶች ሊሰማዎት ይችላል። ከፍተኛ የሆኑ የጎንዮሽ ጉዳቶች እምብዛም አይኖሩም እናም ደህነታቸውን ለማረጋገጥ ከክትባት በኋላ እያንዳንዱ ታካሚ ክትትል ይደረግለታል።

### በምከተብበት ጊዜ የስደት ሁኔታዬ ይወሰዳል?

አይወሰድም። ለመከተብ ማንኛውንም ሚስጢራዊ የግል መረጃዎን ማጋራት አያስፈልግዎትም። ከማህበረሰቡ ጤና ጣቢያ ክትባት መውሰድ ከሚያምኑት ክሊኒክ የጉንፋን መርፌ መውሰድ ወይም መደበኛ ምርመራ ማካሄድ ጋር ተመሳሳይ ነው።

**የኮቪድ-19 ክትባትን እንዴት ዛሬ መውሰድ እንደሚችሉ የጤና ጣቢያዎን ይጠይቁ።**